# ኢሕአፓ የተመክሮ ባለጸጋ
ከታሪኩ ተሰማ

ኢትዮጵያችን በረጅም ታርኳ ዘመን በርካታ አገርንና ሕዝቧን የሚያኮሩ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ጀግና አርበኞችን አፍርታለች፡፡ የሩቁን የአርበኞች ገድል ለታሪክ ትተን ላለፉት ሰላሳዎቹ አመታት በአገሪቷ ታሪክ የመጀመሪያ የጀግንነት ምዕራፍን ስላስመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ስለ ኢሕአፓ መነገር ያለበት ብዙ ገድል አለ፡፡ ኢሕአፓ የዘመናችን ጀግና አርበኛ ስለመሆኑ መጽሃፍ ከመጽሃፍ ሊጻፍለት እንደሚቻል እያመንኩ ያ እውን እስኪሆን ጥቂት በጥቂት ገድሉን ማስቀመጥ የኛ ያለፍንበትና ያለንበት አባላት ግዴታ ነው፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ ስለዚህ ጀግና ድርጅት ጥቂት ላወራ የፈልለኩትና ሌላውም ያለውን እንዲሰነዝር የምጋብዘው፡፡ አባይን በጭልፋ እንዲሉ . . .

ኢሕአፓ የኢትዮጵያን ሕዝብ ላንዴና ለመጨረሻ ነጻ ለማውጣት የፖለቲካ ፕሮግራሙን ለሕዝብ ይፋ በማድረግ በትግል ሜዳው ተሰማርቶ በበርካታ ሺዎች የሚቆጠሩትን አባላቱን ለሕዝብ ነጻነት በማለት ሰውቷል፡፡ በየአቅጣጫው የተነሱበት ፀረ-ሕዝብ ኃይሎች ከፍተኛ ጉዳት ቢያደርሱበትም ቅሉ ኢሕአፓ ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን ሳያጥፍ ዛሬም ከትግሉ ጎራ በሁለገብ የትግል ዘዴው በመታገል ላይ ይገኛል፡፡ የዚህ ጀግና የሕዝብና ያገር ተቆርቃሪ ድርጅት አባልም በመሆኔ ልባዊ ኩራቴ ወሰን የለውም፡፡ አገር አጥፊ ሁሉ እኔ የወያኔ አባል ነኝ ሲል እንዴት ለአገርና ለሕዝባችን እታገላለሁ የምለው ማንነቴን መናገር ይነስብኝ?

ለሕዝባችን ስንል በቀበሌ፣ በከፍተኛ፣ በየፓሊስ ጣቢያዎች፣ በደርግ ጽህፈት ቤት፣ በልዮ ወንጀል፣ ባራተኛ ክፍለጦር፣ በከርቸሌና ባለም በቃኝ ታጉሮ በየጊዜው እንደ ዶሮ የታረደው ና ያለፍርድ የተሰቃየው ያዲስ አበባ የኢሕአፓ አባላትና ባስራ አራቱ ክፍለሃገር በከተማዎች ባውራጃዎች፣ በወረዳዎችና በየቀበሌው የታጎሩትና ደዝባቸው የጠፋው የኢሕአፓ አባላት ቁጥር በመቶ ሺዎች እንደሚቆጠር ይታወቃል፡፡ ሮማውያን በስታዲዮም ውስጥ አንበሳንና የሰውን ልጅ እያታገሉ በሰው ልጅ ስቃይ ይደሰቱ እንደነበር በርካታ የኢሕአፓ አባላትም ላዞ ከነሕይወታቸው እንደተጣሉ ያልሞቱ ያይን ምስክሮች ይኖራሉ፡፡

በልዩ ወንጀል በየጠባቡ ከፍል ታጉረን የሙቀቱ ወላፈን አላስተነፍስ ሲለን አንሶላን ልክ እንደፋን በመጠቀም ተራ በተራ ስናራግብ አሁን ትዝ ይለኛል፡፡ የመኝታ ሰአት ሲደርስ ደግሞ ከመተኛታችን በፊት እንደ ማህንዲስ ቦታ ማደላደልና ያስተኛኘት ዘድዜ መቀየስ ነበረብን፡፡ እንድ ሜትር ባንድ ሜትር የሚሆን ቦታ ለማትረፍ ሌላው ሲተኛ ቢያንስ ቢያንስ አምስት እስረኞች ላንድ ሰአት ያህል ተራ በተራ መቆም ነበረባቸው፡፡ ይህም ተደርጎም ቦታ ስለማይበቃ ሁላችንም የምንተኛው ባንድ ጎን አዱ ወደላይ አንዱ ደግሞ ወደ ታች በመሆን ሲሆን በየመሃላችን የሰውነት ሙቀት ግለትን ለመቀነስ አንሶላ እንደርግ ነበር፡፡ ክርንን ከመንተራስ በስተቀር ትራስ በስምምነት ላለመጠቀም ወስነናል ምክንያቱም ቦታ ያጣብባልና፡፡ ኮርነር ላይ ያሉት ከመተኛታቸው በፊት ግድግዳን ተገን አድርገው ታሳሪውን በሁለት እግራቸው እንደስልቻ በመግፋት ማሽጋሸግና ትንሽም ብትሆን ቦታ ለሚተኛው ወይም ለራሳቸውም ማግግኘት በየምሽቱ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ እንዲያው መድከም እንጂ ባብዛኛው ጊዜ አንድም ስንዝር ትርፍም አይገኝም ነበር፡፡

በየምሽቱ ከልዩ ወንጀል እስር ቤት ከየክፉሉ ላይመለሱ እየተጠሩ የሚወሰዱ ጓዶቻችን ብዛት ቀላል አልነበረም፡፡ በነሱ ቦታ በማግስቱ ባለተራ እስረኛ ይመጣል፡፡ የሚገርመው ግን የሚመጣውም ለሞት የሚሄደውም የነበራቸው ቆራጥነትና አርአያነት ለተፈታነው የኢሕአፓ ጓዶች እስከ ዛሬ ድረስ ስንቅ ሆኖ ያኖረናል፡፡

የተከፈለውን የሕይወት መስዋዕትነት የዘንንድሮዎቹ አራዳ ፓለቲከኞች እንደ ሞኝነት አድርገው ሲይሳንሱት ተደጋግመው ተደምጠዋል፡፡ ያን ከፍተኛ የሕዝብ መስዋዕትነት የተከፈለለትን ሕዝባዊ ትግል ሳያውቁት ቀርተው ሳይሆን በተከፈለው መስዋዕትነት ላይ ወሃ

በመቸለስ በዝሕዝቡ ላይ ያካሄዱትን በደል የሚያጋልጥባቸው ኢሕአፓእን አፍ የዘጉ እየመሰላቸው ነው የሚደክሙት፡፡ እንኳን እነሱ ቀርተው ደርግም ሆነ ወያኔ የኢሕአፓ መስዋዕትነት ሞኝነት ስላለመሆኑ በቅጡ ያውቁታል፡፡

ይልቁኑ የዛሬዎቹ ታጋዮች ስለ ሰላሙ ትግልና ስለ አምጽ ትግል ብዙ ከኢሕአፓ ሊማሩ የሚችሉት ተመክሮዎች በመኖራቸው ሊማሩበት፡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኢሕአፓ ምን ያህል ደርግንና አጃቢዎቹን እንዳርበተበተ ብርሃንና ጨለማ የሚመሰክሩት ሃቅ ነው፡፡ ደርግ ኢሕአፓን ከሕዝቡ ለማቆራረጥ ኢሕአፓ የሱማሌን ጦርነት ደግፏል፡፡ የኢትዮጵያን ሰራዊት ለማጥፋት ጠርሙስ ሰባብሮ በሰ ራዊቱ ራሺን ውስጥ ደባልቋል ተብሎም ነጋ ጠባ ተውርቶ ነበር፡፡ ያኔ የተባለው ዛሬ ስለ ሱማሌ ጦርነት ከሚባለው የሚለይ አልነበርም፡፡ የተባለው ይህ ጦርነት ለጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብና ለሱማሌ ሕዝብ የሚበጅ አይደለም፡ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያትም የደርግና ያጃቢዎቹ የከፋ ጡጫ በኢሕአፓ ላይ ሳያባራ ተካሂዷል፡፡ ኢሕአፓ ደርግን ጠላ እንጅ ላገሩና ለወገኑማ ሲል መስዋዕትነት ከፍላል፡፡ ኢሕአፓ ደርግን ጠላ እንጅ አገሩንና ወገኑን ክዶ ለዛይድ ባረ ጦር አላጎበደደም፡፡ ዛሬም ኢሕአፓ የዘ ድሮውንም የወያኔ ጦር ዘመቻ ሲቃወም ጦርነቱ አላስፈላጊና ምክንያተ-ቢስ መሆኑን ከመጠቆምና የሁለቱንም አገር ሕዝቦች የሚጎዳ ነው ስላለ ሊወነጀል ይሆን? ለነገሩማ ያኔ የኮነኑት ዛሬ የፖለቲካው ሃቅ ተከስቶላቸው ይህን የወያኔን ጦርነት እያወገዙት ይገኛሉ፡፡ መልካም ነው በውነት ከሆነ የሚናገሩት፡፡

በአስር ሺዎቹ የምንቆጠረው የኢሕአፓ አባላት አይተን በማናውቀው የወንጀለኞች እስር ቤቶች ታጉረን በላያችን ላይ የቅማል መንጋ ሲጋልብብን ሽክላ አይሉት ዳቦ ወጥ አይሉት ምናምን እንድንበላ ስንገደድ ከማዘንና ከማማረር ይልቅ ያደረግነ ያን ሲኦል እስር ቤት ውወደ ገነት ነበር የለወጥነው፡፡ ያአይጥ፣ የቅማልና የቁንጫ መፍለቂያ የነበሩ የወንጀለኞችን የሳር ከምር ፍራሾች በማጥፋት፡ መጋቢ ያልነበራቸውን ከየክፍለሃገሩ የመጡትን ወንጀለኞችንንም ሳይቀር አቅርበን ባንድ ላይ ስንቃችንን ተካፍለን ተመግበናል፡፡ በርካታ ወንጀለኞችንም በማስተማር ቢያንስ ሰላማዊ አድርገናቸዋል፡፡ በምሁራን ጓዶቻችን የትምህርት ጥማታችንን እስር ላይ ሆነን ተወጥተነዋል፡፡ ባንድ ወቅት ላይ ኬከርቸሌ የሚወጡ የአስራ ሁለተኛ መልቀቂያ ፈተና ይወስዱ የነበሩ እስረኞች በከፍተኛ ውጤት ወደ ዩኒሸርስቲ እንደገቡ የምናውቀው ሃቅ ነበር፡፡ ያውም በከፍተኛ ነጥብ፡፡

ስንት ጓዶቻችን ነበሩ የእግር ጣታቸው በግርፋት የተበጣጠሰው? በየምሽቱ እየተጠሩ ያልተመለሱትስ ስንቱ እስር ቤት ይቁጠራቸው? በየእስር ቤቶቹ የማጋለጥ ዘመቻ በባለወቅቱ አንጃዎች ሲቃኝ አደገኛነቱን ውስጥ ለውስጥ እያስተማርን የማጋለጥ ዘመቻውን ባብዛኛው ማክሸፋችን የዚያ ወቅት ታሳሪዎች በኩራት የምናስታውሰው ነው፡፡ መርማሪዎች የገደሉትን ለመፍታት የፈቱትን ለመግደል ሲያምሱን እንደነበረም ለታሪክ የሚተው ሃቅ ነው፡፡ ከሚገድሉት ውስጥ ሰው ሲጎድልባቸው መርማሪዎች የወንጀል እስረኞችን የቁጥር ማሟያ ያደረጉበትን ድራማ አስተውለናል በወቅቱ በከርቸሌ የነበርነው፡፡
በየከተማዎቹ የተደረጉት የኢሕአፓ ተጋድሎዎች ለዛሬው ትውልድ በጣም ጠቃሚ ትምህርትና ተመክሮ ያለክፍያ የሚያስገኙ ስጦታዎቹ ናቸው ለሚጠቀምበት፡፡ በጫካ የሰፈረው የኢሕአፓ ሰራዊታችን በርካታ ገድሎችን በደሙ ጽፎ አልፈው አኩርተውናል፡፡ ይህ ጀግና የኢሕአፓ ሰራዊት የሱዳንን ተንኮል፣ የሻቢያና የወያኔን ዱላ ተቃቁሞ ኢትዮጵያዊነቱን ሳይደራረርበት ተዋድቋል፡፡

ኢሕአፓ ስለጋራ ግንባር ትግል አስፈላጊነት አስተምሮ በተግባርም ተሳትፎበታል፡፡ በየጊዜው በባንዳ ምሁራንና ባስመሳይ ተቃዋሚ ድርጅቶች ባገር ላይ የተሴሩትን ድርጊቶች በሙሉ ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን ዳግም እንዳይንሰራሩ አከርካሪያቸውን በጥሶታል፡፡ የተረፉት ደግሞ መልካቸውን ለውጠው እንደሚመጡ ያየነውና የምናየውም ነውና እንዳመጣጣቸውም ምላሽ እንደሚያገኙ እንቆቅልሽ አይደለም፡፡

ኢሕአፓ እልፍ አዕላፍ ጓዶቹንና ደጋፊዎቹን ሰውቷል። ኢሕአፓ ወጣቱን አስጨረሰ ብለው የአዞ እንባ የሚረጩ ገዳዮች የበረከቱበት ዘመን ላይ ደርሰናል። በነሱ ግምት የኢሕአፓ አመራር በግብግቡ መስክ ተሰልፎ ላገርና ለወገን ነጻነት ሲል መሞቱን ቢያውቁም እንኳን የሚመርጡት መካድን ነው ። ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት ሲል ካመራር እስከታች ያሉትን አባላቱን ገብሯል። እንደ ካሃዲዎችና ነብሰበላዎች አባባል ከሆነ ኢሕአፓና ወጣቱ የተለያዩ ተደርገው ቀርበዋል። የድርጅቱንም ምድራዊ ሕይወቱን በመካድ ሰማይ ላይ ተንሳፎ ያለ መንፈስ አድርገው ለማያምናቸው ሕዝብ በከንቱ ለማሳመን መድከም ከጀመሩ ዘመናትን አስቆጥረዋል። ወታቱን አስፈጀ። ሕዝቡን አስፈጀ። የኢሕአፓ ጓዶችን ሞት ግን አይጠቅሱም። ለነሱ በሕዝቡና በጠላት መካከል በሚደረገው ግብግብ ላይ ኢሕአፓ እንደ አልቢትሮ (የጨዋታ ዳኛ) ያውም ከመስኩ ላይ የማይታይ ግን መንፈስ አድርገው ያዩታል አለመታደል ሆኖባቸው። ራሱ ገዳዩ ደርግ እኮ የሚለው ይሕን ያህል ኢሕአፓዎችን ደመሰስኩ እንጂ ኢሕአፓ ያሰማራቸውን ወጣቶች ጨፈጨፍኳቸው አላለም።

ሌሎች ደግሞ የኢሕአፓ አባላት አርጅተዋል ይሉናል በተመክሮ የዳበረና የጠለቀ የፖለቲካ እውቀት አላቸው ላለማለት ብለው። የትግል ዕውቀት ባለጸጋ ስለመሆኑ እያወቁት ግን ሊያጣጥሉት ይከጅላሉ። የፖለቲካ ባለጸጋ በመሆኑ እኮ ነው ዛሬ ኢሕአፓ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅቶች በበለጠ አንጂ ባላነሰ ሕዝቡን ላገሩ ዘብ እንዲቀጥም መመሪያ ሲስጥ ተቀባይነትን ያላጣው። መሪ የሚያደርገውም መሪ ልሁን ብሎ ሳይሆን ተመክሮው ስለሚፈቅድለት ነው። በዘመናት ተመክሮው ስህተቶችን ሰርቶ ሊሆን ይችላል። ቀምነገሩ መሳሳቱን ማራገብ ሳይሆን ተመሳሳይ ስህተቶችን ላለመስራት መጠንጠቀቁ ላይ ነው። እንዲያውም የሕዝብ ወገን ነኝ የሚሉ ድርጅቶች በሙሉ በዕድሜያቸው ለጋ ከሆኑ የኢሕአፓን ተመክሮ ለማዳመጥ ጆራቸውን መክፈት ይጠበቅባቸዋል። ከተመክሮ መማር አያሳፍርም። እንዲያውም አዋቂ ያስብላል።

ይህ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ጨርሶ የማይደራደር የሕዝብ አጋር የሆነ ድርጅት በርታ ሊባልና ሊታገዝ ይገባዋል። በተለይም ደግሞ በተለያየ ምክንያት ግን የድርጅቱ ጠላት ሳይሆኑ ለጊዜ ራሳቸውም ከድርጅቱ ያራቁ የቀድሞ አባላቱ ወደ ድርጅቱ መመለስ ያለባቸው ይመስለኛል። በርግጥ አመላለሱ ቀደም ሲል አንጃው ባቀነባበረው ሴራ አይነት ሳይሆን ድርጅቱ በሚሰጠው መመሪያና ተመላሹም የሕዝብ ወገን ስለመሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ብቻ መሆን ይገባዋል።

የአባይን ውሃና የኢሕአፓን ተመክሮ በጭልፋያ ዘግኖ መጨረስ አይቻልምና የዚህን ታላቅ ጀግና ድርጅት ገድል ሌሎቻችሁም ታቀርቡ ዘንድ እጋብዛለሁ።